# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 34 ታሕሣሥ 30 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!




በቁጥራቸው በጣም ጥቂት የሆኑ ጸረ - ኢትዮጵያ ዘረኞች፣ በሚሊዮኖች የምንቆጠረውን አዋርደው ለመግዛት የበቁት፣ ዛሬም የስልጣን እድሜያቸውን በማራዘም፣ ጸረ ሃገር አጀንዳቸው ማስፈጸም የሚችሉት የተቀረነው ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና ለሃገራችን ደህንነት የምንቆረቆረው ብዙሃኑ የሃገሪቱ ዜጎች አምረን ልንታገላቸው ባለመቁረጣችን ብቻ ነው።

ይህ ትግል ተጀምሯል። ሁሉም የድርሻውን ለማበርከት እየተነሳ ነው። ከመሃላችን ውድ ህይወታቸውን ለመሰዋት ቆርጠው የተነሱ አሉ።

በውጭ ሃገር ከምንገኘው የሚጠበቀው በሕይወታቸው ለቆረጡት የአቅማችንን መደገፍ ነው።

ከእርስዎ የሚጠበቀው የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነው። ሌሎች፣ ኢትዮጵያችንን በህይወታቸው ሊታደጓት ሲነሱ የእርስዎ የገንዘብ እርዳታ ለኢትዮጵያ ሲያንሳት ነው። እኛ ፈዘን ስናቀላፋ የኢትዮጵያ ጠላቶች ያካበቱት ሃብት ብዙ ነው። እነዚህን ዘረኞች ለመታገል፣ ሳንቲም ተለቅሞ አይሆንም። ሁሉም ቀበቶውንና መቀነቱን ጠበቅ አድርጎ ወንዝ የሚያሻግር መዋጮ ማዋጣት ይኖርበታል።

ግንቦት 7 ንቅናቄ በአለም ላይ ከተበተነውና ኢትዮጵያን ከሚወደው እያንዳንዱ ዜጋ 500 የአሜሪካ ዶላር ለማሰባሰብ እቅድ አውጥቷል።

ይህ መዋጮ የወያኔ/ኢህዴግን መጨረሻ ማስጀመሪያ ይሆናል ብለን እናምናለን። ማስጨረሻው ግን ከእዚህም በላይ እንደሚሆን አውቀን ልንዘጋጅ ይገባናል። ምርጫችን ከእነዚህ ዘረኛ አምባገነን ሃይሎች ለመገላገል መክፈል የሚገባንን መስዋእትነት መክፈል ወይም በገዛ ሃገራችን ተዋርደን መኖርና የሃገራችንን ውድምት በጸጋ መቀበል ነው። ይምረጡ! ምርጫዎት ኢትዮጵያና ነጻነት ይሁን። የግንቦት 7 ንቅናቄን የገንዘብ አቅም ለማጎልበት ወገኖችዎትን አስተባብረው ይነሱ። በአስተዋጽዎ ግንቦት 7 ያዘጋጀውን የአርበኝነት የእውቅና ሰነድ የርስዎ ያድርጉ፡፡ ይህ የውርደት ቀን ሲያበቃ፣ ማብቃቱ ደግሞ አይቀርም፣ እኔም ታሪክ ሰርቻለሁ ለማለት ከሚታደሉቱ አንዱ ይሁኑ።




8647 Richmond Highway #652
Alexandria, VA 22309

P.O.Box: 4916, 2003EX
Haarlem, The Netherlands

Tel: +44 208 1335670
www.ginbot7.org


ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከዘረፋው 60 ሚልዮን ብር የደረሳት መሆኑ ተጋለጠ።

የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ከሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት እና መኢአድ ጽህፈት ቤት ፊት ለፊት የሚገኘውን የአዜብ መስፍንን ህንጻ ለአስር አመት በስልሳ ሚሊዮን ብር እንዲከራይ መገደዱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ። ስልሳ ሚሊዮን የሚያክል ገንዘብ ለኪራይ ከመክፈል ከዛ ባነሰ ብር ቴሌኮሚኒኬሽን የራሱን ህንጻ መስራት ይቀለው እንደነበር ምንጮቻችን ገልጸው የተፈለገው የአዜብ መስፍንን ካዝና መሙላት ስለነበር በኪራይ ስም ዘራፋው ተከናውኗል ብለዋል። አይን ባወጣ ሁኔታ የሚዘረፈው የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን መረን በለቀቀ ሁኔታ ሰራተኞቹም ለጥቃት እና ለአስተዳደራዊ በደል መጋለጣቸውን ምንጮቻችን ዘግበዋል።በመስሪያ ቤቱ ሁለት አይነት መዋቅር ሲኖር አንደኛው በችሎታው እና በብቃቱ መስሪያ ቤቱን የተቀላቀለ እና በሀቀኝነት የሚሰራ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ገና ትምህርቱን ሳይጨርስ ቴሌኮሚኬሽን እንደሚቀጠር የሚያውቅ እና የፓለቲካ ታማኝነቱ ብቻ ታሳቢ ተደርጎ የሚቀጠር ነው።ይሄው በፓለቲካ ታማኝነቱ ተመርጦ የገባው ቡድን በመስሪያ ቤቱ ሁለንተናዊ የሆነ የፈላጭ ቆራጭ ስልጣን ያለው እና መስሪያ ቤቱን እንደእንዝርት የሚያሽከረክር ነው ተብሏል።መስራያ ቤቱን በተጠናወተው ሙስና እና ብልሹ አሰራራ የተማረሩ አስራ አምስት አመት በመስሪያ ቤቱ የሰሩ የስራ ሀላፊ ምሬታቸውን ለምንጮቻችን ተናግረዋል።ሀላፊው እንዳሉት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱን በሚያሽከረክሩት የወያኔ ጀሌዎች የተነሳ አብዛኛው የመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ የስራ ፍላጎቱ መሟጠጡ እና መጥፊቱን አስረድተዋል።አብዛኛው ሰራተኛ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ማስታወቂያ

### በውጭ ሃገር የሚኖሩ ልጆች፣ ቤተሰብ ዘመድ ጓደኛ አለዎት?

ዛሬ በግንቦት7 ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች ሃገራችን ወደሌላ የአመጽ አዙሪት እንዳትገባ ከምር ተጨንቀን፣ አንቸኩል! ለወያኔ እድል እንስጠው፤ ግድ የላችሁም እነዚህ ሰዎች የእዚችው ሃገር ዜጎች ናቸው ውለው አድረው ለሀገራችን በጎ መመኘታቸው አይቀረም ብለን ብዙዎች እስከሚታዘቡን መሟገታችንን ----ያውቃሉ?

ሽህ ግዜ ቀናውን፣ ሽህ ግዜ የሰላሙን መንገድ ብንመኘው፣ ሽህ ግዜ እረ ተው፣ ይህች ሃገርና ሁላችንም በጥፋት አዙሪት ውስጥ መድፈቁ ይብቃን ብለን ብንማጸን፤ ከእዚህም አልፎ ተርፎ በታሪካችን አድርገን የማናውቀውን፣ ለሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ተነስተን፣ በሃገራችን ላይ የተሰራውን በደል ወደ ጎን አድርገን፣ በነጻነታችን ተደራድረን ለእረቅ ለስምምነት ጉሮሯችን እስኪደርቅ በመወትወታችን፣ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ያገኘነው ምላሽ፣ እየገዘፈ የሚሄድ ዘረኛነት እብሪትና ንቀት እንደሆነ እርስዎስ ቢሆን ሳይታዘቡት አይቀርም።

እነዚህ ዘረኛ እብሪተኞች ትእግስታችንና ተማጽኗችንን ከፍርሀት የሚቆጥር፣ ያለእኛ ደፋር የለም አንዲሉ አድርጎ የሚያይ በባሩድ ሽታ የሰከረ ህሊና ያላቸው መሆናቸውን እርስዎም እንደኛ ሳይረዱት አይቀርም።

በተደጋጋሚ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ዜጎች ማሰቃየት ማዋረድና ማዋከብ ስራ ብለው ተያይዘውታል። የቅርቡ ሰለባቸው ቴዲ አፍሮ የሆነበት ምክንያት የሚነሳው ከእዚሁ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ ነው። በልምና በምልጃ ስለሰላምና እርቅ በመስበክ የለየላቸው አረመኔዎችን ወደ ቀና ጎዳና መመለስ ይቻላል ብለን እኛ በግንቦት 7 ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖዎችዎ አናምንም። ይህንን እምነታችንን የሚጋሩ ከሆነ! ይነሱ ይቁሙ እኔንም በቃኝ ውርደት ብለው ከቆሙቱ ጎን ቁጠሩኝ ይበሉ።

የግንቦት7 ንቅናቄን ሁለ ገብ ትግል ይደግፉ። ለእዚህ ትግል ማራመጃ ግንቦት ሰባት ይሆን ዘንድ ግንቦት 7 የጀመረውን የገንዝብ ማሰባሰብ ስራ ያግዙ። ሌላውም እንዲተባበር ያስተባብሩ።

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ**

# የመለስ ዜናዊን ጸረ ኢትዮጵያ ጥቃቶች ለመቋቋም አሁንም መፍትሄው ትብብር፣ ትብብርና ትብብር ብቻ ነው

በወያኔ ቁጥጥር ስር ያልሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን፣ የሲቪክ ማህበራትንና የህብረተሰቡን የፖለቲካና የሲቪክና እንቅስቀሴ ለማፈን በመለስ ዜናዊ ሲሸረብ የከረመው የህግ ሴራ በትናንትናው እለት ታህሳስ 28 2001 ቀን ህግ ሆኖ ጸድቋል፡፡ ይህ ህግ በሃገራችን ውስጥ ህገ-መንግስቱንና ህጉን ተገን አድርገው የፖለቲካና የሲቪክ እንቅስቃሴዎች በሚያደርጉ ድርጅቶች እጣ ላይ አስከፊ መዘዝ ይዞ የመጣ ነው፡፡ ይህ ህግ በቀጥታ የሚገድላቸው የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ሲኖሩ ከእዚህ የሚተርፉትም አዝጋሚ በሆነና ስቃይ የሞላው ሞት የሚሞቱበትን ሁኔታ ያመቻቸ ነው፡፡ ይህ ህግ እጅግ አስከፊ ገጽታዎች ያሉት ቢሆንም የእዛኑ ያህል እግራችንን እያነሳን እንድንስቅ የሚያደርግና መለስ ዜናዊ ይሉኝታ የሌለው ዱርዬ መሆኑን የሚያሳይ መረጃም የያዘ ህግ ነው፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ የሃገር ውስጥ የተለያዩ ድርጅቶች ከአጠቃላይ በጀታቸው ውስጥ ከ10 በመቶ በላይ የሚሆነውን ከውጭ ሃገር ምንጮች ማግኘት አይችሉም የሚል ህግ አውጪው መለስ ዜናዊ የራሱ አገዛዝ የአመት በጀት ከ30 በመቶው በላይ የሚሆነው ከፈረንጆች በልመና የሚደጎም መሆኑ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው መለስ ዜናዊ ህጉን ለማወጣት የሰጣቸው ምክንያቶች በሙሉ በቅጥፈት የተሞሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህን አምባገነናዊ ህግ ሊያወግዘው ይገባል፡፡

ከእዚህ ውግዘት ጋር ግን የሃገራችን ዜጎች ልብ ማለት የሚገባቸው፣ ይህ አፋኝ ህግ ለብዙ ወራት ሲሸረብ ቆይቶ አሁን ወያኔን ከሱማሊያ በውርደትና በሽንፈት በሚለቅበት ወቅትና የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን የደረሰባትን የግፍ እስራት በመቃወም ለበርካታ ቀናት የዘለቀ የረሃብ አድማ በማድረግ በምትሰቃይበት ወቅት በገና ዋዜማ የወጣ ህግ መሆኑ ነው፡፡

የወ/ት ብርቱካን ስቃይና የሶማሊያ ጉዳይ የኢትዮጵያውያንንና የአለምአቀፍ ህብረተሰቡን ትኩረት በሳቡበት ወቅት በመለስ ዜናዊ አሽከሮች የተሞላው ፓርላማ ይህንን አፋኝ ህግ በእዚህ ወቅት አጣድፎ ያጸደቀው ያለምክንያት አይደለም፡፡ በርካታ፣ ክፉና መጥፎ ድርጊቶቸን በአንድ ላይ በማከናወን የትኩረት አቅጣጫችንንና የጋራ የተቃው አቅማችንን በመከፋፈል፣ ወያኔ የሚፈጸመውን ወንጀል በጋራ መታገል እንዳንችል ለማድረግ ታቅዶ የተደረገ ስራ ነው፡፡ ይህ ወቅት የተመረጠው ከአንድ በላይ የጥቃት ግንባር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ በመክፈት ለነጻነት ለእኩልነትና ለአንድነት የሚታገለውን ሃይል ብበዙ የጥቃት ግንባሮች ሃይሉን በታትኖ ወያኔን እንዲገጥመው ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ የተቃውሞ እንቅስቃሴያችን በአንድ ጉዳይና በአንድ ግንባር ላይ ሲያተኩር ወያኔ በሌላ ግንባር ጸረ- ኢትዮጵያ ጥቃቱን የለምንም ተቃወሞ ለመፈጸም እንዲችል ነው፡፡ በብርቱካን በቴዲ አፍሮ በሌሎችም ዜጎች በግፍ መታሰር ላይ ትኩረታችንን ጠቅለን ከሄድን ወያኔ ሶማሌን በመውረር፣ በሃገራችን ህዝብ ህይወትና ንብርት እንዲሁም በሱማሌ ውስጥ የፈጸመው ወንጀል ተድበስብሶለት ሊሾልክ ነው፡፡ በሽንፈትና በውርደት ብዙ ወንጀል ፈጽሞ በመሸሽ ላይ መሆኑን ላይነሳበት ነው፡፡ በሶሚሊያ ጉዳይ ላይ እናተኩር ከተባለ በግፍ የታሰሩት ሊረሱ ነው፡፡ ለእነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች ቅድሚያ እንስጥ ከተባለ እነዚህን የወያኔ ድርጊቶች ተከትሎ የጸደቀውን ነጻነትንና መብትን ለማፈን ታቅዶ በወጣው ህግ ላይ ቁጣችን ላናሰማ ነው፡፡

ይህ አይነቱ አሰራር በወያኔ ሆን ተብሎ በስራ ላይ የሚውል መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ የ1997 ምርጫን መጭበርበር፣ የሃገሪቱን ህዝብ በመጨፍጨፍና በገፍ በማሰር፣ የቅንጅት መሪዎችን ቃሊቲ በማጎር፣ ጥያቄያችን የህዝብ ድምጽ ይከበር፣ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ዋስትና የሚሆኑት ተቋማት ይመስረቱ መሆኑ ቀርቶ መሪዎቻችን ይፈቱ ወደሚል እንዲቀየር ሆነ፡፡ መሪዎቻችን ይፈቱ ግድያውና አፈናው ይቁም መለስ ዜናዊ ለፈጸመው ወንጀል ይጠይቅ የሚል ጥያቄያችን አስተባብረን፣ ጉዳያችንም የአለምአቀፍ ህብረተሰቡን ትኩረት ሲስብ ወያኔ ሶማሌን በመውረር ሌላ የትኩረት አቅጣጫ ከፈተ፡፡ አለም አቀፍ ህብረተሰቡ ወደ ሶማሊያ ሲሄድ የእኛ ትኩረት መሪወቻችን ይፈቱ በሚለው ላይ ረግጦ በመቅረቱ ወያኔ በሶማሊያ ለፈጸመውና በሃገራችን ውስጥ በኦጋዴንና በሌላውም አከባቢ በመፈጸም ላይ ለነበረው የግፍ ድርጊት ተገቢ የሆነ ተቃወሟችንን ሳናሰማ ቀረን፡፡ የቅንጅት መሪዎች እንዲፈቱ የተደረገው ትግል ውጤት ሲያመጣ፣ የተፈቱበትን ስምምነትና መንፈስ በማጣመም ከመሪዎቹ መፈታት ጋር ሊፈታ ይገባው የነበረው የታሰረው የዴሞክራሲ ሂደት እንደተሳሰረ እንዲቀር ወያኔ አደረገ፡፡ የቅንጅት መሪዎች ለእስር የዳረጋቸውን የዴሞክራሲ ተቋማት ጥያቄ አንስተው በጋራ በቅንጀት ጥላ ስር እንዳይታገሉ ቅንጅት የሚባለውን ስምና ምልክት ወያኔ ለማይገባቸው አካላት በመስጠት ትኩረታችንን በሙሉ፣ ሁሉ ነገር ቀርቶ ቅንጅት የሚባለውን ስም ለማስለመለስ የሚደረግ ጥረት ብቻ ሆኖ ቀረ፡፡

በእዚህ መሃል ወያኔ የሃገራችን ድንበር ቆርሶ ለሱዳን አስረከበ፤ ይህ ታላቅ ወንጀል ሁላችንንም ሲያስጮህ ወያኔ የተቃወሚ ፓርቲዎችንና ጠቅላላ የሲቪክ ማበረሰቡን ለማፈን የሚያስችለውን ህግ ሲያረቅና ደርጅታዊ አቅሙን ሲያጠናክር ሰነበተ፡፡ ዛሬ ድግሞ ድንበርን አሳልፎ የመስጠት ወንጀል በሌሎች ወንጀሎች ተሸፍኖ፣ በብርቱካን፣ በቴዲ በሌሎችም ዜጎች ላይ በሚፈጸመው የግፍ ወንጀል ትኩረታችን ተስቦ፣ ፊታችንን ወደ ሶማሊያ ዞሮ በላንበት ሁኔታ ይህን አፋኝ ህግ በማውጣት ወያኔ የጥቃት ቀጠናውን እያሰፋብን ነው፡፡ በወጣው ህግ ላይ መግለጫዎች በየአቅጣጫው እያወጣን ነው፡፡ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንና ህብረተሰቡ ትኩረቱ በግፍ ከታሰሩትና ከሶማሊያ ላይ ተነስቶ በወጣው አፋኝ ህግ ላይ መሆኑን የነቢቢሲንንና የአጃንስ ፍራን ፕሬስን የዜና ዘገባዎች ማየት ይበቃል፡፡ የዳር ድንበራችን ጉዳይ አግኝቶ የነበረውን ታላቅ ትኩረት በሌሎች ወያኔ በሚሰጠን የቤት ስራዎች ትኩረት እንዲቀማ ሆኗል፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው የሃገርን ህልውና ጥቅም የማስከበር፣ ነጻናትን ዴሞክራሲንና ፍትህን ለሁሉም ዜጎች የማለበስ ትግል እስካሁን ስናደርገው በነበረው የቆየ የአስተሳሰብና የደርጊት ልምድና ባህል ላይ ቆመን ልናከናውነው የማይቻለን መሆኑን፡፡ በቅድሚያ መለስ ዜናዊ እንዲህ አይነቱን የማያልቅ የግፍና የበደል ጥቃት በሀገራችንና በህዝባችን ላይ እየፈጸመ የሚገኘው አምባገነን በመሆኑ፣ በጎ እስራለሁ ብሎ ግን እየተሳሳ ወያም ካለማወቅና ከድንቁርና የተነሳ አለመሆኑን ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ተዘርዝረው የማያልቁት በሃገርና በወገን ላይ በመለስ ዜናዊ የተፈጸሙ ወንጀሎች ምንጫቸው መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያችንና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሆነ ነገር ካለው፣ ተኮትኩቶ ካደገበት ጥላቻ የመነጨ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ይህ እውቀት ይህን ጸረ-ኢትዮጵያ ግለሰብና ጓደኞቹን ከሃገራችንና ከሁላችንም ጀርባ ላይ ለመንቀል ማድርግ የሚገባንን የትግል መራራነት ያስረዳናል፡፡

መለስ ዜናዊና በዙሪያው ያሰባሰባቸው ጥቂት ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚከፍቷቸውን ማለቂያ ሌላቸው የጥቃት ግንባሮች፣ በሁሉም አቅጣጫ አንዱንም ግንባር ለወያኔ መፈንጫ ሳንተው ተከላክለን መልሰን ወደ አጥቂነት መሸጋገር የምንችለው በሰው ሃይል፣ በገንዘብ፣ በእውቀት የተደገፈ ጠንካር ድርጅት ሲኖረን ብቻ እንደሆነ መሆኑን ያስተምረናል፡፡

ይህ ጠንካራ ድርጅታዊ አቅም ግን ኢትዮጵያን በመሰለ ዘውገ ብዙ፣ ሃይማኖተ ብዙ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍንቶች ብዙና ስብጥር በሆኑባት ሃገር ውስጥ በአንድ ድርጅት ብቻ ሊፈጠር አይችልም፡፡ ወደድንም ጠላንም፣ ሽህ ግዜ ተባብረን መልሰን ሽህ ግዜ ብንሰባበርም፣ ሃገራችንና ሁላችንም ያለንበትን አሳሳቢ ሁኔታ መወጣት የምንችለው በመተባበር ብቻ ነው፡፡ ካለፈው የመተባበር ውድቀት ትምህርት ተምረን መልሰን በመተባበር ብቻ ነው፡፡

ጊዚያዊ፣ ጠባብና የቅርቡን ድርጅታዊ ጥቅም ሳይሆን የመለስ ዜናዊን ጸረ- ኢትዮጵያና አምባገነናዊ አገዛዝ የመጨረሻው የግፍ አገዛዝ በማድረግ፣ ሁላችንም በህግና ልእልና ጥላና በተቋማት ጥበቃ ስር እንክብካቤ በሚደረግላቸው መብቶቻችን አማካይነት በእኩልነትና በነጻነት ልንሰራ፣ ልንኖር፣ ልንደራጅ፣ ልንናገር፣ ልንጽፍ፣ ልናመልክና ለንተዳደር የምንችልበትን ሃገር በሃቀኛ ትብብር ለመገንባት አምረን መነሳት ይኖርብናል፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ‹‹ ይህ የትብብር ግፊት ግን ከጊዚያዊ ስሌት ሳይሆን ከቀን ወደ ቀን እያመረቀዘ አልድን ካለው ቁስል የሚቀሰቀሰውን የሀገራችንና የህዝባችንን ሰቆቃ ማስቆም አለብን ከሚል የሞራል፣ የዜግነትና የሰውነት ግዴታ ከተነሳ ብቻ ነው የታመለትን ግብ መምታት የሚችለው ብሎ ያምናል››፡፡ ለእንዲህ አይነቱ ትብብር መፈጠር ደግሞ የግንቦት 7 ንቅናቄ ሳይታክት እንደሚሰራ በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

## የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ .... (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ በሰገሰጋቸው ካድሬዎች የሀገር አንጡራ ሀብት ሲመዘብር እያየ ክፍኛ እንደሚበግን እና አንዳንዱ ደግሞ ከመናደድም ባሻገር የሚመዘበረውን የህዝብ ንብረት እና የዘራፊዎቹን ማንነት እየመዘገበ በኢትዮድያችን የህግ የበላይነት እና ዴሞክራሲ ሲሰፍን ንበረቱን ለማስመለስ እና ዘራፊዎቹን ለፍርድ ለማቅረብ እንደሚያስብ ተናግረዋል።በቅርቡ ከህግ አግባብ ውጪ ካለምንም ጨረታ ዜድ ቲ ኢ ለተባለ የቻይን ኩባንያ ኔትወርክ ለመዘርጋት እና ለማሻሻል በሚል ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር እንደተከፈለው ሲታወቅ ከአመታት በፊት ይሄው ድርጅት መቀሌ ኔት ወርክ ለመዘርጋት ተስማምቶ ተገቢው ክፍ ያ ከተፈጸመለት በኋላ ይህ ነው የሚባል ስራ አለመስራቱ በደንብ እየታወቀ ለድርጅቱ እንደ ገና የሁለት መቶ ሚሊዮን ብር ስራ ካለጨረታ መሰጠቱ እንቆቅልሽ እንደሆነ ባቸው የስራ ሀላፊው ለግንቦት ሰባት ድምጽ ምንጮች ተናግረዋል።ቻይና እራሷ በሀገሯ የምትጠቀመው ኔር ወርክ ኖኪያ እንጂ ዜድ ቲ ኢ እንዳልሆነ ተገልጾ ወያኔ ይህን ሁሉ የሀገር ሀብት የሚያፈሰው ከቻይና ጋር ግንኙነቱን በኢትዮድያ ህዝብ ኪሳራ ለማጠናከር ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል።

ሃይለ ሀሳብ

## ይድረስ ለወዳጄ

# ከባህር ማዶ ወደ አገር ቤት የተላከ ደብዳቤ

ያኔ አገር ቤት እያለሁ፤ ተደጋግሞ ይለቀቅ የነበረ አንድ የትግረኛ ሙዚቃ፤ ምነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እስከነ አካቴው ቀረ አሉ?ካሴቱ ከድምፅ ሊይብራሪ ውስጥ ጠፍቶ ይሆን ? ወይስ ዜማው "ኤክስፓየርድ" አደረገ? ምንም ትግረኛ ባልችልም ፤ መከላከያ ሠራዊቱ ወደ ሶማሉያ በዘመተ ማግስት ፤በሰፊ አዳራሽ ውስጥ (ምናልባትም በሜጋ አምፊ ቴአትር) በከፍተኛ ዕልልታና ጭፈራ የታጀበውና ያለማሳለስ በየቀኑ በቲቪ ሲለቀቅ የነበረው ዘፈን ፦

" ...ዓለም አሸባርቲ
ዓለም አሸጋርቲ
ጀግናው ተጋዳልቲ
ብሣልሳይ መዓልቲ
ብሣልሳይ ሌሊቲ
ዘፈፃፀመቲ..." የሚል ነበር።ቂቂቂቂቂ........( ቋንቋውን ልታርመኝ ትችላለህ)

የሆነ ሆኖ መልዕክቱ - ዓለምን ያስጨነቁትንና ፣ ዓለምን ያስቸገሩትን አሸባሪዎች፤ ጀግናው ተጋዳላይ በሦስት ቀንና ሌሊት ፀጥ አደረጋቸው መሆኑ ነው። ዘፈኑ አየር ሊይ ከመዋሉ በፊት መለስ ፓርላማው ፊት ቀርቦ " አሸባሪውን ሀይል በአጭር ቀናት ውስጥ አከርካሪውን መትተነዋል"ብሎ ስለነበር፤ ያኔ ሙዚቃውን በምሰማበት ወቅት የግጥሙ ደራሲ እርሱ ይመስለኝ ነበር። ልብ በል! መለስ ፦"ግንባሩን ፈንክተነዋል" ወይም "እግሩን ሰብረነዋል "አልነበረም ያለው።ያለው እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ፤ስብራት እንደሚጠገን፤ የግንባር ቁስልም ሊያጠግ እንደሚችል ስለሚታወቅ ፤ ፍልሚያው ወይም ጦርነቱ እንደተቋጨ የሚያበስር የዕልልታ ከበሮ እንዲያ በአደባባይ ሲጎሰም ባልሰማን ነበር-አዎ! የድል ደስታው በተወሰኑ የገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች ዘንድ ውሀ ልኩን ጥሶ የታየው፤ መለስ ፦ ተጠግቶ የገጠመውን ሳይሆን ፤ ተንደርድሮ የገጠማቸውን ሀይል " አከርካሪያቸው እንደተሰበረ" በማወጁ ነበር።

ይህ ብቻ አልነበረም፤ ገና የውክልና ጦርነቱ ( proxy war) እሽቅድድም በተያዘበት ጊዜ፤ ሠራዊቱ ወደ ሶማሊያ መሰማራቱን አስመልክቶ አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ተቃውሞ በማሰማታቸው ፤ከመለስ የደረሰባቸው ውርጅብኝ ፤ብዙዎችን፦ "የመለስን ቁጣ ያዬ ፤ ቡልቻነትን ባልተመኘ" ወይም " ከሚያሳዬኝ የመለስን ቁጣ፤ በየነነት በአፍንጫዬ ይውጣ"የሚያሰኝ እንደነበር የሚረሳ ታሪክ አይደለም። አዎ! ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የመከላከያ ሠራዊቱን ወደ ሶማሊያ መዝመት አጠንክረው የደገፉ ሰው ቢኖሩ፤ ነፍሳቸውን ይማረውና የኢዴፓው አቶ ልደቱ ብቻ ነበሩ።

እናም... በመለስ አገዛዝ በደረሰበት ተደራራቢ ግፍ በቅርቡ ለህልፈተ ህይወት የተዳረገውና በእውነተኛ የብዕር አርበኞች ልብ ውስጥ ህያው ሆኖ የሚኖረው ዕውቁ ጋዜጠኛ ወንድማችን አብርሐም ረታ ዓለሙ እንዳለው፤ ስንት " ብለን፣ አስብለንና ተብለን " እነሆ የተተፋ ምራቅ ሳይደርቅ፤ ጦሩ ከሶማሊያ ጓዙን ሸክፎ መውጣት ጀመረ-" አይበናንዶ "አሉ ቡልቻ ደመቅሳ?"

በእርግጥ "ጨርሶ ከመቅረት መዘግዬት ይሻላል" እንዲሉ ዘግይቶም ቢሆን አቅምን በማጤን መከላከያ ሠራዊቱን ለማስወጣት ውሳኔ ላይ መደረሱ፤ የወቅቱ ብቸኛ አማራጭ መሆኑ ባያጠያይቅም፤ ከጉዳዩ ጉልህ ፖለቲካዊና አገራዊ መልክ አንፃር አጠቃላይ የሆነው ነገር፤ታላላቅ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ አይቀርም። መቼም ተጠያቂ በሌለበት የምን ጥያቄ ነው የምታነሳው ?እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ።አዎ! አሁን ባይሆንም ወደፊት ጊዜ ሊመልሳቸው ይችላሉና ፤ ምንምና መቼም ቢሆን ፤ ሰዎች ጥያቄያቸውን እንዲያነሱ አትከልክላቸው።እንደውም እንደ አገርም ሆነ እንደ ህዝብ እየጎዱን ካሉት ነገሮች አንዱ ፤ በኩነቶች ዙሪያ ፦" ለምን?" ብለን በአፅንኦት የመጠየቅ ልምድና ባህል አለማዳበራችን እንደሆነ ብዙዎች የሚስማሙበት ነው። በዚህ ከተስማማን እቀጥላለሁ፦

ወዳጄ፦ የወቅቱን የኢትዮ- ሶማሊያ ጉዳይ አስመልክቶ እንደብዙሀን ኢትዮጵያውያን ሁሉ የኔም የመጀመሪያውም ሆነ የመደምደሚያው ጥያቄዬ፦" ለምን ሶማሊያ ውስጥ ተገባ?" የሚለው ነው። " ሠራዊቱ በሶማሊያ ቆይታው ምን አተረፈ? በተለይ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ምን ታጥቶ ምን ተገኘ? እርምጃው ፤ ከአገሮች የሉዓሊዊነት መርህ፣ ከህግና ከታሪክ አኳያስ ትክክል ነበር ወይ? አሁንስ የመውጣት ውሳኔ ላይ የተደረሰው ወትሮ ከነበረው ሁኔታ ምን አዲስ ስኬቶች ተገኝተው ነው?" ወዘተ የሚሉት " ቀድሞውኑ ለምን ተገባ?" የሚለውን አንኳር ጥያቄ ተከትለው የሚፈጠሩ ናቸው።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስዩም መስፍን ለመንግስታቱ ድርጅት ዋና ፀሀፊ ለባንኪሙን በፃፈው ደብዳቤ " ኢትዮጵያ ጦሯን ለማስወጣት የተገደደችባቸውን ሶስት ምክንያቶች አስቀምጣል፦

አንደኛው ምክንያት፤ጦሩ ወደ ሶማሊያ የገባው የመንግስታቱ ድርጅት የሰላም አስጠባቂ ሀይል በአካባቢው እስኪሰፍር ድረስ በሚል ታሳቢ ቢሆንም፤ሌሎች አገሮች ወደ አካባቢው ጦራቸውን ለመላክ ፈቃደኛ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ ተ.መ፣.ድ ሰላም አስከባሪ ሀይል ባለመላኩ፣ ሲሆን

ሁለተኛው ምክንያት ፤ጦሩ የገባው አካባቢው በአስተማማኝ ሁኔታ እስኪረጋጋ ድረስ በሚል እንደሆነና ፤ በዚህም በኩል ዕለት ዕለት የሶማሊያ ቀውስ እየተባባሰ እንጂ እየተሻሻለ ለመጣ ባለመቻሉ ነው ብሏል።

ሦስተኛውና በመጨረሻ ደረጃ በስዩም ደብዳቤ የተጠቀሰው ምክንያት፤ የሽግግሩን መንግስት በተጠናከረ መንገድ ለማቆም በሚል ሀሳብ እንደነበር፤ ሆኖም በዚህም በኩል የሽግግር መንግስቱ ባለስልጣናት የውስጥ ቅራኔያቸውን በመፍታት ወደ አንድ አስተሣሰብ እንዲመጡ የተደረገው ጥረት ተስፋ ሰጪ ባለመሆኑና በኢትዮጵያ ጥረት ሊይ እንቅፋት በመፍጠሩ"ነው ይላል። እንግዲህ ከስዩም ደብዳቤ በግልፅ እንደምንረዳው፤ ጦሩ ወደ ሶማሊያ በሚገባበት ጊዜ በዋነኛነት ታሳቢ የተደረጉት ሦስቱ እቅዶች እውነት ቢሆኑ እንኳ ፤ ከሁለት ዓመት ዘግናኝና አስከፊ ጦርነት በሁዋላ ሶማሊያን እየለቀቀ ያለው፤ ከሦስቱ አንዱን እንኳ ማሳካት ሣይችል ነው።ትርፉ ምን እንደሆነ አንተም፤ እዚህም፤ አገር ቤትም ያለው ወገኔ በደምብ የምናውቀው ነው።አዎ! ትርፉ የወንወድሞቻችን አስከሬን በየጎዳናው መጎተቱ ነው። ትርፉ በጨዋነት ተከብራ ለዘመናት የኖረችውን ክብርት አገራችንን እንደ ወራሪ ማስቆጠርና ማዋረድ ነው።ትርፉ አገራችንን ከመልካም ጎረቤቶቿ ጋር ደም በማቃባት ጠላቶችን ማፍራት ነው። ትርፉ ወደ ግል ኪስ ለሚገባ ዶላር የደሀውን ወታደር መተኪያ የሌለው ህይወት መሸጥ ነው።

ታዲያ ...እዚህ ላይ የስዩም ግልፅነት ሳይገርመኝ አልቀረም ፤ "ለየትኛው ግልፅነት? አፍጠጦ የመጣ እውነታን መቀበል እንዴት ግልፅ ያሰኛል?" እንደማትለኝ ይሰማኛል። አዎ! ስዩም በአሁኑ ጊዜ በሶማሊያ ዙሪያ የፃፈውን ደብዳቤ፤ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማግስት በባድመ ዙሪያ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ አስመልክቶ ከሰጠው መግለጫ ጋር ስታነፃፅረው፤ ሂስን በመዋጥና በግልፅነት በኩል መሻሻል ማሳየቱን ታስተውላለህ።

ሆኖም፤ በሌሎች፤ ማለትም የዲሞክራሲ ካስማ የሆኑት ግልፅነትና ተጠያቂነት በሰፈነባቸው አገሮች ቢሆን ኖሮ፤ይህን የሚያክል ታላቅ አገራዊ ስህተት ፤እንኳን በጓሮ በር በኩል በተደረገ ሂስ መዋጥ፤ ህዝብንም ይቅርታ በመጠየቅ የሚታለፍ አልነበረም።

እኛ አገር ግን ከዚህም የባሰ ቢፈፀም ችግር የለውም- ምክንያቱም ተንቀናል፤ እኛም ተኝተናል።
ግን፣ግን ተኝተናል ነው የሚባለው? ወይስ ዝገናል?
መልሱን ላንተ ትቸዋለሁ።
ለማኝኛውም ጦማሬን በሚቀጥሉት ስንኞች ልቋጭ፦

እልል ዕንበል,

እሪታችንን እናምቀው- እልልታችን ያስተጋባ፣
እንደልማዳችን እንዝፈን- እንበል ጎሮ ወሸባ፣
ምንም በድል ባይመለስ- ጀግናው በሽንፈት ቢገባ።
እልልልል,,,,,,,,,

ከግንቦት 7 ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የወ/ት ብረቱካን መዲቅሳን መታሰር አስመልክቶ ከግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

በትናንት እለት ታህሳስ 20 2001 አ.ም የመለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በወ/ት ብርቱካን መዲቅሳ የወሰደውን በእብሪት የተመላ የእስራት ርምጃ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አጥብ ያወግዛል:: በእዚሁ አጋጣሚ የእብሪት አገዛዙ በቅርቡ በወይዘሮ መሰበወርቅ ቅጣው የመኢአድ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ፣ በአቶ በቀለ ጅራታ የኤሮሞ ፌደራሊስት ፓርቲ ጸሃፊ እንዲህሁም በሌለች የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት ላይ የወሰደውን ተመሳሳይ የአፈና አርምጃ ግንቦት ሰባት አጥብቆ ይኮንናል:: ከእዚህ በተጨማሪ አገዛዙ የተለያዩ ድርጅቶችን አበላትና ደጋፊዎች ማንገላታትና ማፈኑን፣ ዜጎችን በዘራቸው እየለዬ በጅምላ የእስራት ርምጃ ማሰቃየቱን የግድያ ርምጃ መውሰዱን የግንቦት 7 ንቅናቄ አምሮ ይቃወማል::

ንቅናቄያችን በተለያዩ ወቅቶች የመለስ አገዛዝ የሚፈጽመውን የግፍ ድርጊት የሚኮንኑ መግለጫወች ማውጠቱ ቢታወስም የወይዘሪት ብርቱካን በግፍ መታሰር ምክንያት በማድርግ ይህንን መግለጫ ለማውጣት የተገደደበት የራሱ ምክንያት አለው:: የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አካላት መሃል የተወሰኑቱ እንደ ወ/ት ብርቱካን በቅንጅት መሪነታቸው በግፍ የታሰሩና እንደ ወ/ት ብርተካን እንዴት ከእስር እንደተፈቱ ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው፣ የአንድነት ሊቀመንበሯ ይህንን ከእስር የመፈታት ሂደት በሚመለከት የሰጡት የቃል ይሁን የጽሁፍ መግለጫ አንዱም ስንኝ ሳይቀር በውቅቱ የሆነውን ሃቅ የሚያነጻባርቅ ትክክለኛ መሆኑን የምስክርነት ቃል ለመስጠት ነው:: የወ/ት ብርቱካን መግለጫ እንኳን በሃሰት ክስ ላይ የተመሰረተና በይቅር እንባባል መንፈስ የተሰረዘን ፍርደ ገምድላዊ የእድሜ ልክ እስራት የሚስያጀመር ቅጣት ቀርቶ በፖሊስ አስጠርቶ ሊያስጠይቅ የማይገባው ጉዳይ እንደሆነ ግነቦት 7 ለሚመለከተው ሁሉ መሳወቅ ይወዳል::

ይህ በትናንትናው እለት በወ/ት በርቱካንና ከእዛም በፊት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አበላት ላይ የተወሰደ የእብሪት እርምጃ ያነጣጣረው በሃገራችን ውስጥ ለዴሞክራሲ መከበር ትግላቸውን ህግንና ሰላምን አጥብቀው በመያዝ የሚያደርጉትን አካላት እንቅስቃሴ ሲቻል ለመግደል ባይቻል ለማዳከም በመለስ አገዛዝ ሆን ተብሎ በስራ ላይ እየዋለ ያለ ፖሊሲ መሆኑን ሁሉም ሊያውቀው ይገባል:: እንዲህ አይነቱ የስርአቱ የእብሪት እርምጃ ጾታን እድሜን ዘርንና ሃይማኖትን ሳይለይ በሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለ በደል መሆኑን በመረዳት ይህንን ማስቆም የሚቻለው ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች በጋራ ሲኮንኑትና አገዛዙን በጋራ ሊታገሉት ሲችሉ ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል::

በእዚሁ አጋጣሚ ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት መገንባትና ለሰብአዊ መብት መከበር ቆመናል የሚሉ መንግስታትና የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ይህ በሃገራችን አየተፈጸመ ያለ የወንብድና ርምጃ አንዲቆም ማድረግ የሚቻላቸውን ሁሉ አርምጃ እንዲወስዱ ግንት 7 ጥሪውን ያቀርባል:: በእዚህ ፈታኝ ወቅትም በሃገርና በሃገር ውስጥ የሚኙው የሃገሪቱ ዜጋ በሙሉ በመለስ አገዛዝ ለሚሰቃዩ የተለያዩ የፖለቲካ ደርጅቶች መሪዎች አበላትና ዜጋ በሙሉ አጋርነቱን በሚቻለው መንገድ ሁሉ እንዲያሳይ ወገናዊ ጨሁኸቱን ግንቦት 7 ያደርሳል::

# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

# ወያኔ እንደለመደው አልሸባብን የሚዋጋ ተለጣፊ የእስላማዊ ቡድን በመርዳት ላይ ነው::

በ2 አመቱ የሱማሊያ ወረራ የአልሸባብን ሽማቂዎች ማሸነፍ ተሰኖት አገሪቱን በከፋ ቀውስ ውስጥ ከቶ የወጣው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፣ የሱማሊያን ህዝብ ስቃይና መከራ ለማራዘም ሌላ ትናንሽ ቡድኖችን ለማስታጠቅና የርስ በርስ ግጭቱን ለማስፋፋት የሚያስችል እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን የውጭ ጉዳይ ምንጮቻችን ከኬንያ የወያኔ ኤምባሲ አካባቢ በተገኘው መረጃ አረጋገጡ ::

በሶማሊያ እየተጠናከሩ የመጡትን የአልሸባብ ቡድን መቋቋም ያቃተው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሶማሊያን ለቆ እየፈረጠጠ ባለበት ሰአት ሌላ ሶማሊያን ወደ በለጠ ጦርነት እካባቢውንም ወደ ከፋ አለመረጋጋትና ሽብር ውስጥ ለማስገባት በሶማሊያ የሚገኙ ትንንሽ ቡድኖችን ማስታጠቅ መጀመሩን በኬንያ ያሚገኘው አምባሳደር ለወያኔ አለቆቹ ከላከው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል::

እንደመረጃው ከሆነ ‘አሁሉ ሱና ዋል ጃማህ’ የሚባለው ቡድን መሪ በናይሮቢ ሰጡት በተባለው መረጃ ድረጀታቸው የአልሸባብ ቡድንን መዋጋት መጀመሩን እንዲሁም የአልሸባብ ቡደን እየተከፈለና እየተዳከመ የመጣ ቡድን መሆኑን ጠቅሰው ኢትዮጵያ እርዳታ ብታደርግልን ወጤታማ እንሆናለን በማለት ጥሪ ያቀረቡ መሆኑን በኬንያ የወያኔ አምባሳደር “ዲሳሳ ድሪብሳ ለውጭ ጉዳይ ሚንስቴር አለቆቹ በላከው ደብዳቤ አረጋግጦአል:: እንደ ውስጥ አዋቂዎቻችን መረጃ “እነዚህን የተለያዩ ሱማሌ አንጃዎችን መርዳትና ማስታጠቅ መንግሥታቸው (ወያኔ )የሚያራምደወን አላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳል” የሚል አረፍተ ነገር በደብዳቤው ውስጥ መካተቱንና ይህም በኬንያ የሚገኘው የሥር ዓቱ እምባሴ ሴራውን ከግብ ለማድረስ ሃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ያመላክታልም ተብሎአል::

በጉዳዩ ላይ ዘጋቢያችን አስተያየት እንዲሰጡ የጠየቃቸው አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሙሁር እንዳሉት “ኢትዮጵያውያን ራሱ ወያኔ በፈጠረው ችግር በረሀብ እየተሰቃዩ ባለበት ሰአትና ለማይረባ የፖለቲካ ጥቅም ብሎ የብዙ የኢትዮጵያንን ውድ ህይወትና በመከራ የተገኘ የእርዳታ ገንዘብ በሶማሊያ ለፈጸመው ኢፍትሀዊ ወረራ ሲገበር የቆየው አልበቃ ብሎት በቀጣይነት በሶማሊያውያን የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ በመገባት ልፈትፈት ማለቱ እጅጉን የሚያሳዝን ነው:: እነሱ ያልተረዱት ሀቅ ግን ይህ እርምጃ እነሱ ሀገርቤት ውስጥ እየተፈጠረባቸው ያለውን ችግር የሚያባብስና ወደባስ ውደቀት ውስጥ የሚከት መሆኑን ነው” ብለዋል::

የወራሪው ሠራዊት ከሱማሌ መውጣት ከመጀመሩ በፊት መለስ ዜናዊ በቅርቡ በሰጠው የተለመደ የቃላት ኮማንዶው “ሰሞኑን ከሶማሊያ በመውጣት በኢትዩጵያ ድንበር ላይ ሆነን አልሸባብን እንከላከላለን” ማለቱ የሚታውቅ ነው:: እንደተለያዩ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት ወያኔ እንድህ ዓይነቱን ምስቅልቅል የሚፈጠረው በርግጥ እልሸባቦች ቢያንስ በዚህ ደረጃ ለኢትዮጵያ ሰጋት አለመሆናቸው ጠፍቶት ሳይሆን በዚህ ወር መጨረሻ ላይ ሰልጣን ላይ የሚወጣውን አዲሱን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ አባማን አቋም ለማየትና እንደበፊቱ ገንዘብ የሚያገኝ መሆኑን እርገጠኛ የሚያደርገው ምልክት ሲያገኝ ተመልሶ የፈረደባቸውን ወታደሮች ኢፍትሀዊ ወደ ሆነ የጦርነት እሳት ውስጥ ለመማገድና የሚገኘውንም ጥቅም እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ጥቂት የወያኔ ሹማምንት ኪስ ማደለቢያ ሊያደረጉት መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው ተብሎአ።

በኬንያ የሚገኘውም አምባሳደር ዲሳሳ ድሪብሳ የላከው ደብዳቤ ይዘትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሀቅ ነው ያሉት እንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የተቃዋሚ ፓርቲና የይስሙላው ፓርላማ አባል በማስቀጠልም በሶማሊያ የተፈጠረው ችግር ለወያኔ ከፈተኛ የገቢ ምንጭ እንደሆነላቸው በመግለጽ ወደፊትም በሶማሊያ የእርስ በርስ ብጥብጡን በማስፋፋት ለአሜሪካ መንግስትና ለአለም ማህበረሰብ ችግሩን ሊፈታ የሚችል ዝግጁ ሀይል የነሱ ጦር መሆኑን ለማስገንዘብ ብሎም የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ለማግበስበስ ነው:: በፊት እንዴት ሶማሊያ አትግቡ ትላላችሁ ብሎ ሲያብጠለጥለን ከርሞ አሁን ደግሞ ራሱ ልውጣ ማለቱ ያስተዛዘበን ሲሁን እሁን ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መግባት አለብኝ ብሎ ፓርላማው እንዲያጸድቅለት መጠየቁ የማይቀር ነው ሲሉ አስተያየታቸውን እጠናቀዋል::